# በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ የኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት እና መዛግብት

መንግሥቱ ጎበዜ*

## ፩.መግቢያ

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባለቤት ናት፡፡ ብዙዎቹ የአገሪቱ ባህላዊ ቅርሶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ይዞታ ሥር የሚገኙ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ በርከት ያሉ ባህላዊ ቅርሶችን በዓለም አቀፍ ቅርስነት በማስመዝገብ በአፍሪካ በግንባር ቀደምነት ትጠቀሳለች፡፡ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ ሳይንስ እና ባህል ድርጅት/UNESCO/ ከተመዘገቡት ስምንት ዓለም አቀፍ ቅርሶች ውስጥ ሰባቱ ባህላዊ ቅርሶች ናቸው፡፡[1]

ይኽንና ከሰባቱ ባህላዊ ቅርሶች ሌላ አገራችን ዐሥራ ሁለት የሥነ ጽሑፍ ሀብቶችን በዓለም ቅርስነት አስመዝግባለች፡፡ እነዚህ ቅርሶች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምህራን እና ሊቃውንት ብራና ፍቀው፣ ብዕር ቀርጸው እና ቀለም በጥብጠው ለትውልድ ያበረከቷቸው የብራና መጻሕፍት እና መዛግብት ናቸው፡፡ የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ዓለምአቀፍ የሥነ ጽሑፍ ቅርሶቻችንን ማስተዋወቅ እና ጠንክሮ መሥራት ከተቻለ ሌሎች በርካታ ሀብቶቻችንን በዓለም ቅርስነት ማስመዝገብ እና ተጠቃሚ መኾን እንደሚቻል ማመልከት ነው፡፡

ይህ ጽሑፍ ከብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት እና ቤተ መዛግብት ኤጀንሲ በማይክሮ ፊልም የተነሡትን ጨምሮ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍትን እና መዛግብትን በመመልከት፣ ከዓለም አቀፍ የሥነ ጽሑፍ ቅርሶቻችን ጋር በተያያዘ የተደረጉ የደብዳቤ ልውውጦችን፣ የተሠሩ ሥራዎችን፣ የቅርስ ማኅደሮችን በመዳሰስ እና ከሚመለከታቸው የኤጀንሲው ሠራተኞች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተጠናከረ ነው፡፡[2] ከዚህ በተጨማሪ ስለ ዓለም አቀፍ ሥነ ጽሑፍ ቅርሶች አመዘጋገብ እና መስፈርት እንዲሁም የአገራችንን የሥነ ጽሑፍ ቅርሶች እና ልዩ ልዩ ጽሑፎች ለመመልከት ተችሏል፡፡

## ፪. ከድንጋይ ወደ ብራና

የታሪክ እና የአርኪዎሎጂ ምሁራን በዓለማችን ላይ የጽሑፍን መጀመር የቅድመ ታሪክ እና የታሪክ ዘመናት መለያ አድርገው ይወስዱታል፡፡ ጽሑፍ ከመጀመሩ በፊት ያለውን *ቅድመ ታሪክ* ሲሉት፣ ከዚያ በኋላ ያለውን ደግሞ *ዘመነ ታሪክ* ይሉታል፡፡ የሰው ልጅ ጽሑፍን የጀመረው ከዛሬ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት በፊት እንደ ነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡[3] እነዚህ መረጃዎች በድንጋይ ላይ ተጽፈው የተገኙ በመኾናቸው የሰው ልጆች ጽሑፍን የጀመሩት በድንጋይ ላይ እንደ ነበር ምስክሮች ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ሐሙራቢ የተባለው የባቢሎን ንጉሥ በሁለት ሺህ ዓመተ ዓለም ገደማ በጥቁር ድንጋይ ላይ ሕጎችን ቀርጾ መገኘቱ ለአብነት የሚጠቀስ ነው፡፡[4]

*መንግሥቱ ጎበዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአርኪዎሎጂና የቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር ናቸው፡፡

[1] ስምንቱ ዓለም አቀፍ ቅርሶች የሚባሉት የቅዱስ ላሊበላ አብያተክርስቲያን፣ የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ የጎንደር አብያተ መንግሥት፣ የአክሱም የአርኪዎሎጂ እና የታሪክ ቅርሶች፣ የጥያ ትክል ድንጋዮች፣ የታችኛው አዋሽ እና የኦሞ ሸለቆ የቅድመ ታሪክ ጥናት መካናት እና የጀጎል ግንብ/ሐረር/ ናቸው፡፡ ከተፈጥሮ ቅርሶች የሚመደበው የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ብቻ ነው፡፡

[2] በዚህ ረገድ የተባበሩኝን የኤጀንሲውን ሠራተኞች መሪጌታ ብርሃኑ አበራን፣ ወ/ሮ ኅሊና ሥዩምን፣ ወ/ሪት አዳነች ሥዩምን እና አቶ ዮሴፍ ደምሴን ላመሰግን እወዳለኹ፡፡

[3] Douglas Price and Gary M Feinman, *Images of the Past*, (Myfield Publishing Company: 1997), p..394

[4] Joseph P. Free,. *Archaeology and Bible History*, (wheat Illinios: Van Kampen Press,1952,) pp. 94-95

የነቢያት አለቃ ሙሴ በተመሳሳይ ዘመን ዐሥርቱ ትእዛዛት የተጻፉበትን ሁለት የድንጋይ ጽላቶች በሲና ተራራ ከልዑል እግዚአብሔር እንደተቀበለ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል፤[5] በአገራችንም በቅድመ አክሱምም ኾነ በዘመነ አክሱም በለሰለሰ ድንጋይ ላይ ተጽፈው የሚገኙ የሳባ እና የግእዝ ፊደላት ጽሑፎች አያሌ ናቸው። በዚህ ረገድ በአምስተኛው ዓመተ ዓለም በሳባውያን ፊደል በድንጋይ ላይ ተቀርጾ የሚገኘው ጽሑፍ፣ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሦስት ቋንቋዎች/በሳባ፣ ግእዝ እና ግሪክ/ ፊደላት ተቀርጾ የተገኘው የንጉሥ ኢዛና ጽሑፍ /Ezana Inscription/ ዐይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው።[6]

ከብዙ ጊዜ በኋላ ሰዎች የተለያዩ የቤት እና የዱር እንስሳት ቆዳዎችን ፍቀው፣ በልዩ ልዩ መሣሪያዎች አለስልሰው፣ ልክ እንደ ወረቀት አድርገው ካዘጋጁ በኋላ ሐሳባቸውን በጽሑፍ ላይ ማስፈር ጀምረዋል። ይህ ለፊደላት መሣያ /ማስቀመጫ/ የሚዘጋጀው ለስላሳ ሰሌዳም ብራና በመባል የሚታወቀው ነው። የብራና ላይ ጽሑፍ በዓላማችን ላይ መቼ እንደተጀመረ ለማወቅ አዳጋች ቢኾንም ነቢያት[7] እና ሐዋርያት[8] ለመጻፊያነት ብራናን ይጠቀሙ እንደ ነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ።

በአገራችን የብራና ላይ ጽሑፍ በአክሱም ዘመነ መንግሥት እንደተጀመረ የሚገመት ሲኾን ከዚያም በዛጉዌ ዘመነ መንግሥት እና በተለይም ደግሞ በመካከለኛው የታሪክ ዘመን የበለጠ ዳብሮ መገኘቱን ለመረዳት ተችሏል።[9] እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአገራችን በጥንታዊነት ከሚታወቁት የብራና መጻሕፍት መካከል በአባ ገሪማ ገዳም /ትግራይ/ የሚገኘው አርባዕቱ ወንጌል ዋነኛው ነው። ይህ ብራና በድንቅ ሥዕሎች ያሸበረቀ እና የአባ ገሪማ ወንጌል በመባል የሚታወቅ ሲኾን ከ፮ኛው-፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ተጻፈ ይታመናል።[10]

---

[5] ኦሪት ዘጸአት ፳፬፥፲፪-፲፬

[6] Mengistu Gobezie, *Heritage Tourism in Ethiopia*, (Addis Ababa: BSPP, 2008.) , pp.124-125. በአገራችን የሚገኙ ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ ላይ የዋለው የሳባ ቋንቋ ሲኾን ከዚያም ግእዝ እንደተከተለው ይታመናል:: ኾኖም የግእዝ ቋንቋም ኾነ ፊደል ከሳባውያን በኋላ ተገኘ ብሎ ለመናገር አያስደፍርም። ጉዳዩ ራሱን የቻለ ሰፊ ጥናት እና ምርምር ሊካሄድበት የሚገባ ተግባር ነው።

[7] ኤርምያስ ፴፮፥፳፪-፳፬

[8] ሉቃስ ፬፥፲፬፤ ፪ኛ ጢሞ ፬፥፲፫

[9] ፈቃደ ሥላሴ ተፈራ/ሊቀ ጉባኤ/፣ *ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት አዘገጃጀት.* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኘሬስ አዲስ አበባ(፳፻፪ ዓ.ም) ምዕራፍ ፪

[10] ደሴ ቀለብ /መምህር/፣ *ትንሣኤ ግእዝ፡* (አዲስ አበባ፤ ማኅበረ ቅዱሳን፣ /፳፻፪/ ገጽ ፶፮ በርግጥ በቂ ጥናት ባለመደረጉ ሊኾን ይችላል እንጂ የብራና መጻሕፍት በአገራችን ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደነበሩ የሚጠቁሙ ማስረጃዎች አሉ። ለምሳሌ በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው በንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሳለ /በ፴፬ ዓ.ም/ የነብዩ ኢሳይያስን መጽሐፍ/ምዕራፍ ፶፫/ ሲያነብ ሐዋርያው ፊልጶስ እንደተመለከተው ይተርካል/የሐዋ. ሥራ ፰፥፳፮-፵/። ጃንደረባው ምናልባት ይህን መጻሕፍ ከኢትዮጵያ/ከሀገሩ/ ወስዶት ሊኾን ይችላል። ያ ከኾነ ደግሞ መጽሐፉ ሊኾነ የሚችለው የብራና ነው። ከዚህ ሌላ በርካታ መንፈሳዊ መጻሕፍት ከልዩ ልዩ ቋንቋዎች በአባ ፍሬምናጦስ/የመጀመሪያው የኢትዮጰያ ጳጳስ/ እና ኋላም በዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ግእዝ ቋንቋ መተርጐማቸውን የታሪክ ሰነዶች ምስክር ናቸው። ከእነዚህም መካከል መጽሐፈ ኄኖክ እና መጽሐፈ ቀለሜንጦስ ለአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

## ፫. የኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት እና መዛግብት አጠቃላይ ሁኔታ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እና መምህራን እንደ ብራና፣ ብዕር እና ቀለም የመሳሰሉትን የጽሑፍ መሣሪያዎች አዘጋጅተው ፊደላትን ቀርጸዋል፤በዚህም ምክንያት ድንቅ በኾነው የእጅ ሥራቸው ለትውልድ የተሻገሩ አያሌ የብራና መጻሕፍትን አበርክተዋል። እነዚህ ሊቃውንት እና መምህራን በዚህ ድንቅ ተግባራቸው ሃይማኖታቸውን፣ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን እና ቅርሳቸውን ለትውልድ ከማውረሳቸውም ባሻገር አገራችን ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ተለይታ የምትታወቅበት የራሷ የኾነ ሥነ ፊደል እና ሥነ ጽሕፈት እንዲኖራት ያደረጉ ባለውለታዎች ናቸው። ስለኾነም ኢትዮጵያ በጥንታዊ የብራና መጻሕፍት ክምችት ከሚታወቁ የዓለም አካባቢዎች አንዷ ስትኾን እስከ አሁን ድረስ ከግማሽ ሚልዮን የማያንሱ ብራናዎች እንዳሏት ይታመናል።[11] በርካታዎቹ የብራና መጻሕፍት በአገራችን ልዩ ልዩ ገዳማት፣ አድባራት እና የገጠር አብያተ ክርስቲያን ይገኛሉ። በቀላል ቁጥር የማይገመቱ ደግሞ በግለሰቦች እጅ እና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከአገር ወጥተው በሌሎች አገሮች እንደሚገኙ ይታወቃል።

በኢትዮጵያ የሚገኘው የብራና ሥራ የብራና አወጣጥን፣ የቀለም እና የብዕር አዘገጃጀትን፣ የፊደል አጣጣልን፣ የነጥብ አቀማመጥን፣ የቀለም ቅብን፣ የሐረግ እና የሥዕል ንድፍን፣ ጥረዛ እና ድጎሳን የሚያጠቃልል ክቡር ሞያ ነው። ሊቃውንቱ ይህን ብራና ዳምጠው፣ ቀለም በጥብጠው፣ ብዕር ቀርጸው በእጅ የሚያከናውኑትን የጽሕፈት ሞያ *ቁም ጽሕፈት* በማለት ይጠሩታል።[12]

የአገራችን የብራና መጻሕፍት ዘርፈ ብዙ ሃይማኖታዊ እና አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ናቸው። በተለይም ደግሞ የእነርሱ መገኛ ለኾነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖቷ፣ ሥርዐቷ እና ትውፊቷ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ። በተመሳሳይ መልኩ መንግሥታዊ ዐዋጆች፣ ሕጎች፣ ደንቦች እና ትእዛዞች ወደ ኅብረተሰቡ እንዲደርሱ እና እንዲሰሙ በማድረግ፤በውጭ ግንኙነቱም በደብዳቤ ልውውጥ የዲኘሎማሲን ሥራ ለማከናወን ታላቅ አገራዊ እገዛ ማበርከታቸው ታሪክ የማይረሳው እውነታ ነው። በቀደሙት ዘመናት ብዙ ውሎች ተጽፈው የሚገኙት በብራና መዛግብት ስለነበር ዛሬ ድረስ ተጠብቆ ለቆየው ምስክርነታቸው ታላቅ ጠቀሜታ ነበራቸው።[13] ዛሬም ቢኾን የብራና መዛግብቱ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትምህርቷን፣ሥርዐቷን እና ትውፊቷን ለማስተላለፍ፣ ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን ለመፈጸም እና ለጸሎት አገልግሎት የሚውሉ ከመኾናቸውም ባሻገር፣ ለታሪክ ማስረጃነት፣ ለምርምር ሥራ ምንጭነት፣ በቅርስ ሀብትነት እና የቱሪዝም መስሕብ በመኾን ያላቸው ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በአገራችን የሚገኙ የብራና መጻሕፍት እንደ ቁጥራቸው ሁሉ ዐይነታቸውም የተለያየ ነው።[14] ስለኾነም እጅግ ጥቂቶቹ ለምሳሌ እና ለግንዛቤ ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል።

---

[11] አበባው ይግዛው/ሊቀ ማዕምራን/፣ *የቁም ጽሕፈት ሙያ በኢትዮጵያ* ፣ (ለንደን፤ ዳሽን ኘሪንቲንግ ኢንተር ኘራይዝ ፣ /፲፱፻፺፱/ ገጽ ፲፯

[12] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፰-፱

[13] ፈቃደ ሥላሴ ተፈራ ፣ገጽ ፮-፯

[14] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አጭር የታሪክ፣የሃይማኖትና የሥርዐት መጽሐፍ።* (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያቤት፣ /፲፱፻፸፫/ ገጽ ፰፰-፸፱

| የነገረ ሃይማኖት መጻሕፍት | የዜማ መጻሕፍት | የቤተክርስቲያን አስተዳደር መጻሕፍት | የዘመን አቆጣጠር መጻሕፍት | ታሪክ ጠቀስ መጻሕፍት | የፍልስፍና መጻሕፍት |
|---|---|---|---|---|---|
| ሃይማኖተ አበው | ድጓ | መጽሐፈ ሲኖዶስ | መጽሐፈ አቡሻኽር(ቁጥር) | ድርሳነ ጽዮን | ወግረስ ጠቢብ |
| መጽሐፈ ባሕርይ | ጾመ ድጓ | ዲድስቅልያ | ሰዒድ ወልደ ባጥሪቅ | ዜና አይሁድ | አንጋረ ፈላስፋ |
| መጽሐፈ ሐዊ | ምዕራፍ | አብጥሊስ | ማርቆስ ወልደ ቀንበር | ታሪክ ነገሥት | ሐተታ ዘርዓያዕቆብ |
| ህላዌ መለኮት | ዝማሬ | ፍትሐ ነገሥት | መርሐ ዕውር ዘድሜጥሮስ | ብዕለ ነገሥት | መጽሐፈ ቅኔያት |
| መጽሐፈ ምስጢር | መዋስዕት | ፈውስ መንፈሳዊ | ባሕረ ሐሳብ | ክብረ ነገሥት | |
| ርቱዓ ሃይማኖት | ዚቅ | ድርሳን ዘርክበ ካህናት | | ገድለ አዳም | |
| | ቅዳሴ | | | ዜና እስክንድር | |
| | ሰዓታት | | | | |

ሠንጠረዥ ፤

የኢትዮጵያ የብራና መዛግብት በአብዛኛው በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ እና ዕድሜ ጠገብ ናቸው። ይኹንና የተጻፉበትን ዘመን ለመለየት በጣም አዳጋች ነው። ለዚህም ሦስት ዐበይት ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

የመጀመሪያው፣መዛግብቱ የተጻፉበትን ወይም የተተረጎሙበትን ዓመት ይዘው አለመገኘታቸው ነው።[15] ምንም እንኳ ጥቂቶቹ በተጻፉበት ወይም በተተረጎሙበት ዘመን የነበረውን የንጉሥ ወይም የመስፍን ስም ይዘው ቢገኙም አንዳንዴ የተፋቁ እና በሌሎች ስሞች የተተኩ ስለሚኾኑ ተአማኒነቱ ያነሰ ይኾናል። ሁለተኛው ችግር ደግሞ አብዛኞቹ መዛግብት የደራሲያቸውን ወይም የተርጓሚያቸውን ስም ይዘው አለመገኘታቸው ነው። የቀደሙት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምህራን እና ሊቃውንት ከንቱ ውዳሴን በመጥላት ወይም በደረሱትም ኾነ በተረጐሙት የብራና መጽሐፍ ላይ ስማቸውን አይገልጹም - ይኸውም ስለ ትሕትናቸው ነው። ሌላው መጻሕፍቱ ራሳቸው በዕድሜ ብዛትም ይኹን ከአቀማመጥ እና ከአያያዝ ጉድለት የተነሣ በደረሰባቸው ጉዳት እና ብልሽት ምክንያት ጽሑፋቸው ሊነበብ ያለመቻሉ ነው።

ምንም እንኳ ሙሉ በሙሉ ቀርቷል ባይባልም ለዘመናት በብራና ላይ ሲከናወን የቆየው የቁም ጽሕፈት ሥራ ዛሬ ዛሬ በአገራችን እየተዳከመ መምጣቱ የሚካድ አይደለም። በበርካታ ገዳማት እና አድባራት ሥራው እየቀረ በመሄዱ ምክንያት ሞያውም እየተረሳ መጥቷል። ለዚህም የማተሚያ ቤቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ እና ቀደም ብሎ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች በብራና ላይ በእጅ ይጻፉ የነበሩ መጻሕፍትን በኮምፒዩተር ጽሕፈት እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በዲጅታል ካሜራዎች እያነሡ እንደ ልብ በማተሚያ ቤት ማሳተም እና ማባዛት መቻሉ፣ የግእዝ ቋንቋ ዕውቀት መዳከም እና በቤተክርስቲያን አካባቢ ተወስኖ መቅረቱ፣ በዘመናችን የሚጻፉት አብዛኞቹ መጻሕፍት ትኩረታቸው ዓለማዊ ጉዳዮች ላይ መኾኑ እንደ ምክንያት ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው።[16]

## ፬. በዓለም ቅርስነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መስፈርቶች

ዓለም አቅፍ ቅርሶች የሚባሉት ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶችን አሟልተው የሚገኙ፣ በሚመለከተው ዓለም አቀፍ ድርጅት ታይተው በዓለም ቅርስነት የሚመዘገቡ የሰው ልጆች ሁሉ ሀብቶች ናቸው። ለዓለም አቀፍ ቅርሶች ዕውቅና መስጠት፣ መመዝገብ፣ መቆጣጠር እና መከታተልን በተመለከተ ሓላፊነት ያለው ዓለም አቀፍ ተቋም የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት(UNESCO) ነው፤ በሥሩም በርካታ ድርጅቶችን አቅፎ ይዟል። ከእነዚህም መካከል “ሜሞሪ ኦፍ ዘወርልድ ሬጅስተር” (Memory of the World Register) የሚባለው አንዱ ነው። ይህ ድርጅት የሥነ ጹሑፍ ቅርሶችን(Documentary Heritage) በመመዝገብ፣ በመከታተል እና በመቆጣጠር በኩል ሓላፊነት የተሰጠው አካል ነው። ተቋሙ በተለያዩ አገሮች የሚገኙ መዛግብታዊ ቅርሶች ዓለም አቀፍ መስፈርትን አሟልተው በእጩነት ከቀረቡ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገቡ ያደርጋል፤ ዋና ዋና መስፈርቱም ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው።

**፬.፩. ተአማኒነት(Authenticity)፡-** ይህ መስፈርት መዛግብታዊ ቅርሱ፣ ጥንተ ማንነቱን እና መሠረታዊ ባሕርይውን ይዞ መገኘቱን ወይም ከሌላ የተገለበጠ፣ ቅጅ ያልኾነ ወይም መስሎ የተዘጋጀ አለመኾኑን በማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው።

---

[15] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አጭር የታሪክ፣የሃይማኖትና የሥርዐት መጽሐፍ።* ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያቤት፣ አዲስ አበባ/፲፱፻፸፰/ ገጽ ፳፰-፸፱

[16] ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት መስፈርቶች ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት እና ቤተ መዛግብት ከተገኘው Memory of the World፡ General Guidelines to Safeguard Documentary Heritage ከሚባለው የዩኔስኮ ሰነድ የተገኙ ናቸው።

**፬.፪. አምሳያ እና ምትክ የሌለው መኾኑ**[17]/Unique and Irreplaceable/፡- ይህ መስፈርት ቅርሱ በዐይነቱ ልዩ እና ጉዳት ቢደርስበት ወይም ቢጠፋ እንኳ የማይተካ መኾኑን የሚመለከት ነው። በዚህ መስፈርት መሠረት የቅርሱ መጎዳት ወይም ጨርሶ መጥፋት በሰው ልጆች የቅርስ ሀብት ላይ ትልቅ ጉዳት እና ክፍተት የሚፈጥር ነው።

**፬.፫. ሌሎች ግምት ውስጥ የሚገቡ መስፈርቶች**

- ሀ/ **ጊዜ**፡- ቅርሱ የተዘጋጀበትን ዘመን ልዩ ኹኔታ መግለጽ መቻሉ ወይም በዘመኑ ለተከናወኑ ጉልሕ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ክሥተቶች በማስረጃነት ለመግለጽ ብቸኛ አማራጭ መኾኑ፣
- ለ/ **ቦታ**፡- ይህ መስፈርት ቅርሱ ከተዘጋጀበት ወይም ከተገኘበት ቦታ ጋራ ያለውን ትስስር ይመለከታል። የቅርሱ መገኛ ቦታ በዓለም ታሪክ ወይም ባህላዊ ሂደት ውስጥ ትርጉም ያለው ሚና መጫወቱን ወይም ቦታው በራሱ በቅርሱ ውስጥ ለተጠቀሱት ወሳኝ ክሥተቶች ትልቅ ተጽዕኖ ያለው መኾኑን ማስገንዘቡ ፤
- ሐ/ **ሕዝባዊ ሚናው**- ቅርሱ ሲዘጋጅ በነበረበት ወቅት የነበረውን ማኅበረሰብ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ሥነ ጥበባዊ. . . ወዘተ ዕድገት ቅርሱ መግለጥ መቻሉ ወይም ቅርሱ ስለ ታላላቅ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች፣ ዕድገቶች፣ ለውጦች፣ ስፍኻት. . .ወዘተ መረጃ ሊሰጥ መቻሉ፣ በተጨማሪም በአንድ የታሪክ አጋጣሚ ጉልሕ ሚና ስለነበራቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እንቅስቃሴ መረጃ መስጠት መቻሉ፤
- መ/ የቅርሱ **ርእሰ ጉዳይ** እና **ጭብጡ** እንዲሁም ቅርሱ **በቅርጹ** እና **ይዘቱ** የላቀ ነገር የሚታይበት መኾኑ

**፬.፬. ሌሎች ተጨማሪ ጉዳዮች፤**

- ሀ/ **በብዛት የማይገኝ መኾኑ**(Rarity)፡- ቅርሱ የትም ቦታ የማይገኝ እና አነስተኛ ቁጥር ያለው መኾኑ፣
- ለ/ **የተሟላ መረጃ መስጠቱ**(Integrity)፡- መዛግብታዊ ቅርሱ በርካታ ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ ችግሮችን አልፎ ሙሉ ኾኖ መገኘቱ እና የተሟላ መረጃ መስጠት መቻሉ፣[18]
- ሐ/ **ስጋት**(Threat)፡- ቅርሱ በአስቸጋሪ ሁኔታ መገኘቱና ያለበት አጠቃላይ የደህንነት ጉዳይ አሳሳቢ በመሆኑ ጥበቃና ትኩረት የሚያሻው መሆኑ፣
- መ/ **የቅርሱ አጠባበቅ ዕቅድ**(Management Plan)፡- አንድን መዛግብታዊ ቅርስ ለዓለም አቀፍ ቅርስነት እንዲመዘገብ ለማድረግ የቅርሱን ጠቀሜታ፣ አጠቃቀም፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ በጠያቂው አካል ዕቅድ መዘጋጀት መቻሉ።

## ፭. በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ እና በእጩነት የቀረቡ የብራና መጻሕፍት እና መዛግብት

አገራችን ኢትዮጵያ በረጅም ጊዜ ታሪኳ ያፈራቻቸው በርካታ ባህላዊ ቅርሶች አሏት። ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹ ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶችን አሟልተው በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (UNESCO) በዓለም ቅርስነት ተመዝግበው ይገኛሉ።[19] ይኹን እንጂ በርካታ ኢትዮጵያውያን በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡትን የብራና መዛግብት ያውቋቸዋል ብሎ ለመናገር አያስደፍርም።

---


[17] በዚህ ረገድ ግሸን ደብረ ከርቤ ገዳም ብቻ የሚገኘውን መጽሐፈ ጤፉት እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል።
[18] ቦታ የሚባለው ነገር አካባቢን፣ ከተማን ወይም ተቋምን ሊወክል ይችላል።
[19] ማስታወሻ 1'ን ተመልከት

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ በተገኘው መረጃ መሠረት፣ አገራችን ዐሥራ ሁለት የብራና መዛግብትን በዓለም ቅርስነት አስመዝግባለች፡፡ ስድስቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለሃይማኖታዊ አገልግሎት ይውሉ የነበሩ፣ ሦስቱ ነገሥታቱ ለውጭ መንግሥታት የላኳቸው ደብዳቤዎች እና ሦስቱ ደግሞ የታሪክ እና አስተዳደር ቀመስ መጻሕፍት ናቸው፡፡[20]

| *ተ.ቁ* | *የመዛግብቱ ስም* | *የተጻፈበት ዘመን* | *መግለጫ* |
|---|---|---|---|
| 1. | አርባዕቱ ወንጌል | ፲፬ኛው | የሐዲስ ኪዳን ክፍል የኾኑትን የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስ እና የዮሐንስ ወንጌልን የያዘ መጽሐፍ ነው። |
| 2. | የጳውሎስ መልእክት | ፲፫ኛው | የሐዲስ ኪዳን ክፍል የኾኑቱን ፲፬ቱን የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ያቀፈ መጽሐፍ ነው። |
| 3. | መዝሙረ ዳዊት | ፲፬ኛው | መቶ ኀምሳ መዝሙራትን የያዘ፣ በእስራኤሉ ንጉሥ ዳዊት እንደተደረሰ የሚታመን እና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ምእመናን ለጸሎት የሚገለገሉበት፣ የአብነት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ ንባብን ለመለማመድ የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ነው፡፡ |
| 4. | ግብረ ሕማማት | ፲፫ኛው | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰሙነ ሕማማት የሚነበብ ከሐዲስ እና ከብሉይ ኪዳን የተውጣጡ ጥቅሶችን የያዘ ትልቅ መጽሐፍ ነው፡፡ |
| 5. | መጽሐፈ ሄኖክ | ፲፫ኛው | ሄኖክ የአዳም የልጅ ልጅ ከኾኑት የመጽሐፍ ቅዱስ አበው አንዱ ሲኾን መጽሐፉም ከተጻፈበት ዘመን ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ በዚህ ዓለም ላይ ስለሚኾነው ማናቸውም ነገር የሚናገር የትንቢት መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በሌሎች ዓለማት ጠፍቶ በኢትዮጵያ ብቻ መገኘቱ ይታወቃል፡፡ |
| 6. | መጽሐፈ ቅዳሴ | ፲፯ኛው | የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምትጠቀምባቸው ፲፬ቱ ቅዳሴያትን አጠቃሎ የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ |
| 7. | የዳግማዊ ምኒልክ ታሪክ | ፲፱ኛው | ይህ መጽሐፍ በንጉሡ ዘመን በነበሩት በጸሓፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የተጻፈ የዳግማዊ ምኒልክ ታሪክ ነው፡፡ |

[20] ስለ እነዚህ በዓለም ቅርስነት ስለ ተመዘገቡ የብራና መዛግብት መረጃ የተገኘው ከብሔራዊ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተባበሩኝን የኤጀንሲውን ሠራተኞች መሪጌታ ብርሃኑ አበራን፣ ወ/ሮ ኀሊና ሥዩምን፣ ወ/ት አዳነች ሥዩምን እና አቶ ዮሴፍ ደምሴን ላመሰግን እወዳለኹ፡፡ እንዲሁም በቅርስ ልማት ጥናት እና ጥበቃ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ባለሞያ የኾኑትን አቶ ተስፋዬ አራጌን አመሰግናለኹ፡፡

| ተ.ቁ | የመዛግብቱ ስም | የተጻፈበት ዘመን | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 8 | ነገሥት | ፲፱ኛው | ለበርካታ ዓመታት ኢትዮጵያውያን ሲተዳደሩበት የነበረ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ ጉዳዮችን የያዘ የሕግ መጽሐፍ ነው። |
| 9 | ታሪከ ነገሥት | ፳ኛው | የመጽሐፉ ይዘት በአብዛኛው ስለ ዓመተ ዓለም አቆጣጠር፣ ስለ ኢትዮጵያ ነገሥታት እንዲሁም በአራተኛው እና አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኒቂያ፣በኤፌሶን፣ በቁስጥንጥኒያ እና በኬልቄዶን ስለተደረጉ የሃይማኖት ጉባኤዎች እና ክርክሮች የሚያስረዳ ነው። |
| 10 | ዐፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት ደብዳቤ | ፲፱ኛው | የደብዳቤው መንፈስ የቱርኮችን ጥቃት ለመቋቋም፣ የእንግሊዝን ርዳታ ስለ መሻት የተጻፈ ነው። |
| 11 | ዳግማዊ ምኒልክ ለሞስኮው ቄሳር ዳግማዊ ኒኮላስ የጻፉት ደብዳቤ | ፲፱ኛው | የደብዳቤው አጠቃላይ መንፈስ እስላማዊ ኀይሎች የኾኑት ግብጽ እና ቱርክ በጠረፍ አካባቢ የፈጠሩትን ስጋት በተመለከተ ከሩስያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን መንግሥት ጋራ ተባብሮ መሥራትን ይመለከታል። |
| 12 | የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ለእንግሊዝ ንግሥት የጻፉት ደብዳቤ | ፲፱ኛው | ንጉሡ ሣህለ ሥላሴ የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ አያት የኀይለ መለኮት አባት ሲኾኑ ከ፲፰፻፭-፲፱፻፵ ዓ.ም. የሸዋ ንጉሥ ነበሩ፤ የደብዳቤያቸውም መንፈስ የእርሳቸው እና የእንግሊዝ መንግሥት ወዳጅነት እንዲመሠርት፣ የሁለቱም አገሮች ነጋዴዎች በሰላም እና በወዳጅነት መንፈስ እንዲዘዋወሩ እና እንዲነግዱ የሚያስችል ስምምነት ነው። |



ዐርባዕቱ ወንጌል /በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈ/
*ምንጭ፦ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ*
*የውጭ እና ሕዝብ ግንኙነት፣ ፈለገ ጥበብ፡፡ ግንቦት 2002*

ከላይ ከተገለጹት መዛግብት በተጨማሪ ሌሎች ሦስት ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት በዓለም ቅርስነት ለመመዝገብ በእጩነት ቀርበዋል፤ መጻሕፍቱም መጽሐፈ ጤፉት፣ ርቱዐ ሃይማኖት እና መጽሐፍ ቅዱስ ናቸው፡[21]

<u>መጽሐፈ ጤፉት</u>፡- ይህ መጽሐፍ በ፲፬፻፵፯ ዓ.ም በንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ትእዛዝ እንደተደረሰ ይታመናል፡፡ መጽሐፉ ስያሜውን ያገኘው በፊደላቱ ደቃቅነት እንደ ኾነ ሲነገር ዋና ይዘቱም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀል ከውጭ ስለመምጣቱ፣ ለሦስት ዓመታት የሚያርፍበት መስቀለኛ ተራራ ሲታሠሥ ከቆየ በኋላ በግሸን ዓምባ ላይ ማረፉን የሚያስረዳ ነው፡፡ ለእጩነት የቀረበው ይህ መጽሐፍ በሁለት ዐምድ በግእዝ ቋንቋ የተጻፈ እና መጠኑም ፳፩ በ ፲፯ ሣ.ሜ የኾነና ፪፻፳፯ ገጾች ያሉት ነው፡፡ መጽሐፈ ጤፉት ወደ አገራችን ከመጣው እና ግሸን ደብረ ከርቤ ከሚገኘው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀል እና በዘመኑ ከነበረው ከንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ጋራ የተገናኘ በመኾኑ ያለውን ታሪካዊ ፋይዳ የጎላ ያደርገዋል፡፡

<u>ርቱዐ ሃይማኖት</u>፡- ይህ መጽሐፍ ስለ ነገረ ሃይማኖት የሚያብራራ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ በ፲ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአገራችን ወደ ግእዝ ቋንቋ እንደተተረጐመ ይታመናል፡፡ የመጀመሪያው(Original) ብራና የሚገኘው በጣና ቂርቆስ ገዳም ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በሁለት ዐምዶች በግእዝ ቋንቋ የተጻፈ እና ፪፻፪ ቅጠሎች ያሉት ነው፤ መጠኑም ፵.፰ በ ፴.፰ ሣ.ሜ ነው፡፡ ርቱዐ ሃይማኖት በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም በማይክሮፊልም ተነሥቷል፡፡


<u>መጽሐፍ ቅዱስ</u>፡- ይህ መጽሐፍ ከ፲፱፻፳፪-፲፱፻፳፮ ዓ.ም ድረስ ለአራት ዓመታት ያህል በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ በብራና የተገለበጠ ነው፡፡ መጽሐፉ ብሉይ እና ሐዲስ የሚባሉ ሁለት ክፍሎች ሲኖሩት እያንዳንዳቸው በሁለት ዐምዶች፣ በግእዝ እና በአማርኛ ቋንቋዎች የተጻፉ ናቸው፤ መጠናቸውም ብሉይ ኪዳኑ ፵፰ በ ፴፫ ሣ.ሜ ሲኾን ሐዲስ ኪዳኑ ደግሞ ፵፩ በ ፴ ሣ.ሜ ነው፡፡ መጽሐፉ በጥቅል ወደ ፩፻ የሚደርሱ የፍየል ቆዳዎችን እንደ ፈጀ ይነገራል፡፡

[21] ዝኒ ከማሁ

ከላይ የተገለጹት ሦስቱ የብራና መጻሕፍት ከ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ በዓለም ቅርስነት ለመመዝገብ በእጩነት የቀረቡ ቢኾንም እስከ አሁን ግን ከመዝጋቢው አካል የመጣ ይፋዊ መልስ የለም። ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ መረዳት እንደተቻለው ሰኔ ዘጠኝ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በቁጥር ዮፓ/፬፱/፺፯፣ ፓሪስ በሚገኘው በ'ዩኔስኮ ሜሞሪ ኦፍ ዘወርልድ ሬጅስተር' የተጻፈ ደብዳቤ፣ ያልተሟሉ ነጥቦች በመኖራቸው የእነዚህ መጻሕፍት ምዝገባ ሂደት በአንድ ዓመት እንደተራዘመ ያመለክታል። በሌላ በኩል ከኤጀንሲው ሠራተኞች መረዳት እንደተቻለው መዝጋቢው ዓለም አቀፍ ድርጅት ማይክሮፊልም የተነሣውን የርቱዐ ሃይማኖት መጽሐፍ ኤጀንሲውን ጣና ቂርቆስ ከሚገኘው ዐይነተኛው (original) መጽሐፍ ጋራ እንዲያመሳክር ቢጠይቅም፣ "ለመስክ ሥራ የሚኾን በጀት የለም" በሚል ሰበብ ሥራው አለመሠራቱ ታውቋል።

## ፫ ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን አሟልተው በዓለም ቅርስነት ሊመዘገቡ የሚችሉ በርካታ የብራና መዛግብት እንዳሏት ይታወቃል። እስከ ዛሬ ድረስ የተመዘገቡት እና በእጩነት የቀረቡት መዛግብት ከአገራችን የብራና መጻሕፍት ብዛት እና ዐይነት አኳያ ሲነጻጸር እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ ብቻ እንኳ ከ፲፯ሺሕ በላይ በማይክሮፊልም የተነሡ፣ ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ የማያንሱ ደግሞ በጥንታዊ የመዛግብት እና የኢትዮጵያ ጥናት አገልግሎት አሰጣጥ(በግእዝ) ክፍል ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል በግምት ከ፴፫-፵ ኪሎ ግራም የሚመዝነው፣ ፱፻፸፪ ገጾች ያሉት በአማርኛ እና ግእዝ ቋንቋዎች የተጻፈው ትልቁ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ይገኛል።[22]



ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ የበግ ቆዳ የፈጀ የብራና መጽሐፍ
ምንጭ፦ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ የውጭ እና ሕዝብ ግንኙነት፣ ፈለገ ጥበብ፡፡ ግንቦት 2002

[22] ይህ መጽሐፍ በዐፄ ኀይለ ሥላሴ ትእዛዝ በቤተ መንግሥት በአራት የቁም ጽሕፈት ባለሞያዎች አምስት ዓመት ፈጅቶ የተጻፈ ነው። በአጠቃላይ ወደ ፪፻፵፱ የበግ ቆዳ እንደ ፈጀ መሪጌታ ብርሃኑ አበራ ገልጸዋል። መሪጌታ ብርሃኑ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ የጥንታዊ ግእዝ ክፍል (የመዛግብት እና የኢትዮጵያ ጥናት አገልግሎት አሰጣጥ ክፍል) የሚሠሩ ባለሞያ ናቸው።

ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ትኩረት ተሰጥቶ ቢሠራበት ቀድመው ከተመዘገቡት ይልቅ ጥንታዊነት ያላቸው እና የመመዝገቢያ መስፈርቶቹን የበለጠ ሊያሟሉ የሚችሉ አያሌ የብራና መዛግብት በአገራችን ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህል አስቀድሞ የተገለጸውን በአባ ገሪማ ገዳም የሚገኘውን አርባዕቱ ወንጌል መጥቀስ ይቻላል፡፡

ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያላቸውን ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት በዓለም ቅርስነት ከማስመዝገብ ጋራ በተያያዘ ሦስት መሠረታዊ ችግሮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው፣ ተገቢውን መረጃ አሰባስቦ ቅርሶቹን ለእጩነት እንዲቀርቡ ለማድረግ አለመቻል ነው፡፡ ብራናዎቹ በራሳቸው ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን አሟልተው መገኘታቸው ብቻ ለዓለም ቅርስነት አያበቃቸውም፡፡ ዝርዝራቸውን በሚገባ ለይቶ ማስመዝገብ ብዙ ድካም የሚጠይቅ እና ውስብስብ ሂደት ያለው ነው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ በመስፈርቱ መሠረት ብቁ የኾኑትን መዛግብታዊ ቅርሶች መምረጥ፣ አጠቃላይ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ለዚህም ተገቢውን ቅጽ መሙላት፣ ለውድድር እና ለእጩነት እንዲቀርቡ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ እና ሂደቱን እስከ መጨረሻው ድረስ መከታተል እንዲሁም በማከታተል በሚቀርቡት ጥያቄዎች መሠረት የጎደሉ ነገሮችን ማሟላት ዐበይት ተግባራት ናቸው፡፡

ሁለተኛው፣ ቅርሶች በዓለም ቅርስነት ቢመዘገቡ ያላቸውን ጠቀሜታ በአግባቡ መረዳት ያለመቻል ነው፡፡ ቅርሶችን በዓለም ቅርስነት ማስመዝገብ ለአንድ አገር በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ቅርሶቹ ራሳቸው በደንብ እንዲታወቁ፣ ሕጋዊ ከለላ እና ክብካቤ እንዲደረግላቸው ያግዛል፡፡ በመታወቃቸው ምክንያት በጎብኚዎች ሊታዩ እና አጥኚዎችም ለምርምር ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ቅርሶቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመዝግበው መያዛቸው እና መታወቃቸው ለአገር ገጽታ ግንባታ ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡ የጐብኚዎች መስሕብ በመኾንም ለአገር የምጣኔ ሀብት ዕድገት የበኩላቸውን ድርሻ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡

በሦስተኛ ደረጃ፣ አብዛኛው የብራና መጻሕፍት በልዩ ልዩ ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች ችግር ላይ በመኾናቸው አስፈላጊውን መረጃ አሟልቶ ለእጩነት ለማቅረብ ከባድ ሥራን የሚጠይቅ መኾኑ ነው፡፡ በአገራችን በልዩ ልዩ አድባራት እና ገዳማት የሚገኙ የብራና መጻሕፍት በዕድሜ ብዛት፣ ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋላቸው፣ በአጠቃቀም ችግር፣ በአያያዝ እና አቀማመጥ ጉድለት፣ በጐብኚዎች የፎቶ ካሜራ ብርሃን (Flash)፣ በዘረፋ እና በስርቆት፣ በሕገ ወጥ ዝውውር[23] እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ጥፋታቸው እና ጉዳታቸው እየተባባሰ ሄዷል፡፡ በተለይ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቀላል ቁጥር የማይገመቱ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት ገጾቻቸው በድጅታል ካሜራዎች እየተነሣ በመካነ ድር(website)[24] በኩል ለሽያጭ እየቀረቡ መኾናቸው የብዙዎቹን ዐይነተኛ (Original) ጽሑፍ ለማግኘት አስቸጋሪ እየኾነ መጥቷል፡፡

በአጠቃላይ አገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ድንቅ ሃይማኖታዊ ቅርሶች ማኅደር እንደ ኾነች ቢታወቅም በልዩ ልዩ ምክንያቶች አገራችንም ትኹን ቤተ ክርስቲያናችን በተገቢው ኹኔታ ተጠቃሚ መኾን አልቻሉም፡፡ በዚህ ረገድ ጥንታዊ የብራና መዛግብቱ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ስለዚህም እነዚህን ድንቅ ሀብቶች በተገቢው አኳኋን ጠብቆ ተጠቃሚ መኾን ይቻል ዘንድ እነርሱን በመንከባከብ፣ በማስተዋወቅ፣ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገቡ በማድረግ እና በመሳሰሉት ቀና ተግባራት ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ይገባል፡፡

---

23 ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ በተገኘ ደብዳቤ ቁጥር 1/UNESCO-019/01-033/97 የካቲት 14 ቀን 1997 መሠረት ኢትዮጵያም ሕገ ወጥ የባህላዊ ቅርሶችን ዝውውር ለመከላከል እ.ኤ.አ በ1970 ዓ.ም የጸደቀውን ዓለም አቀፍ ስምምነት ፈርማለች፡፡

24 በዚህ ረገድ ‘eBay’ የሚባለውን መካነ ድር ማየት ይቻላል፡፡